የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ—ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 16
ADDIS ABABA - 8th December, 1998

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፱/፲፱፻፺፩ ዓ·ም·
ከጅቡቲ አዲስ አበባ ስለተዘረጋው የምድር ባቡር ከጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተደረገውን ስምምነት ለማሻሻል የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ............... ገጽ ፱፻፲፩

CONTENTS

Proclamation No. 135/1998
Agreement for the Amendment of the Agreement with the Republic of Djibouti regarding the railway line laid between Djibouti and Adddis Ababa Ratification Proclamation ......................... Page 911

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፱/፲፱፻፺፩

## ከጅቡቲ አዲስ አበባ ስለተዘረጋው የምድር ባቡር የተደረገውን ስምምነት ለማሻሻል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ከጅቡቲ አዲስ አበባ ስለተዘረጋው የምድር ባቡር መጋቢት ፲፪ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ·ም የተደረገውን ስምምነት ለማሻሻል የሚያስችል ስምምነት የካቲት ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም ጅቡቲ ላይ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ከጅቡቲ አዲስ አበባ ስለተዘረጋው የምድር ባቡር ከጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተደረገውን ስምምነት ለማሻሻል የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፱/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO139./1998

## A APROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT CONCLUDED BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBIC OF DJIBOUTI

WHEREAS, an Agreement for the amendment of the Agreement concluded on March 21st 1981 regarding the railway line laid between Djibouti and Addis Ababa was signed at Djibouti on the 23rd of February, 1997 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on the 8th day of December, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Agreement for the Amendment of the Agreement with the Republic of Djibouti regarding the railway line laid between Djibouti and Addis Ababa Ratification proclamation No. 139/ 1998."

፪· <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

መጋቢት ፲፪ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ.ም ከጅቡቲ አዲስ አበባ ስለተዘረጋው የምድር ባቡር የተደረገውን ስምምነት ለማሻሻል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የካቲት ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጅቡቲ ላይ የተፈረመው ስምምነት ጸድቋል።

፫· <u>የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ሥልጣን</u>

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከህዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት



2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti for the amendment of the Agreement concluded on March 21st,1981 regarding the railway line laid between Djibouti and Addis Ababa is hereby ratified.

3. *Power of the Minister of Transport and Communications*

The Ministry of Transport and Communication is hereby empowered to take necessary measures for the implementation of the agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force on the 8th day of December, 1998.

Done at Addis Ababa, on the 8th day of December, 1998

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE